የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ—ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 12
ADDIS ABABA - 24th Nov., 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፭/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
ለዓለምገና – ቡታጅራ መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፰፻፺፭

## CONTENTS

Proclamation No. 135/1998
African Development Fund Loan Agreement for Financing the Alemgena-Butajira Road Upgrading project Ratification Proclamation ...................................... Page 895

### አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፭/፲፱፻፺፩
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለዓለምገና — ቡታጅራ መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ዩ.ኤ. ፲፰ሚሊዮን ፭፻ሺህ (አሥራ ስምንት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ዩኒትስ አፍ አካውንት) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትየጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፰ በአቢጃን የተፈረመ በመሆኑ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለምአቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ
ይህ አዋጅ "ለዓለምገና – ቡታጅራ መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፭/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION 135/1998
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 18,500,000 UA (eighteen million five hundred thousand Units of Account) for financing the Alemgena – Butajira Road Upgrading project, was signed in Abidjan, on the 21st day of July, 1998;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 24th day of November, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
This Proclamtion may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for Financing the Alemgena-Butajira Road Upgrading project Ratification Proclamation No. 135/19

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ «የብድር ስምምነት» ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፰ በአቢጃን የተፈረመው ቁጥር ኤፍ/ኢቲኤች/አርኦዲ–ዩፒጂ፺፰/፴፱ የብድር ስምምነት ነው።

፫. <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ዩ.ኤ. ፲፰ ሚሊዮን ፭፻ ሺህ (አሥራ ስምንት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ ዩኒትስ አፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. F/ETH/ROD-UPG/98/39 signed in Abidjan, on the 21st day of July, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of UA 18,500,000 (eigtheen million five hundred thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 24th day of November, 1998.

Done at Addis Ababa, this 24th day of November, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE